በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 15 ቀን 2009 ዓ.ም

# የትምህርት ጥራት መውደቅ የወያኔ ፖሊሲ መዝቀጥ ነፀብራቅ ነው።

ትምህርት የዕድገትና የስልጣኔ መሰረት ነው። ለአንድ አገር የኢኮኖሚ ብልጽግና የሚገኛው ችግር ፈቺ የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት ሲቻል ነው። የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ደግሞ አገራዊ ራዕይ ያለው የአገሪቱን የባሕልና የልማድ ሁኔታን ባገናዘበ መልክ የባለድርሻ አካላት በሆኑት መምህራን፣ ወላጆች፣ ተማሪዎች፣ መንግስትንም ጭምር ያካተተ ሕዝባዊ የትምህርት ፖሊሲ ሲቀረጽ (ሲዘጋጅ) ብቻ ነው። የትምህርት ሥርዓት ባለው ላይ እየተጨመረ ለከታታይ ትውልድ በሚበጅ መልኩ የአገሪቱን የፖለቲካ ፣የኢኮኖሚና የሶሻል ሁኔታ ተመርኩዞ እንደ አገሪቱ የዕድገት ደረጃ የሚሻሻል እንጂ መንግስት በተለወጠ ቁጥር ወይም በተቀየረ ጊዜ አብሮ የሚለወጥ መሆን የለበትም ( አይደለም)። አለመታደል ሆኖ ደርግ የአጼውን ወያኔ ደግሞ የደርግን የትምህርት ፖሊሲ በመቀየር ለራሱ የጎሣ ፖለቲካ ማራመጃ በሚጠቅም መልኩ ማደራጀቱ ይታወቃል።

የወያኔ መንግስት የጉዳዩን ባላቤቶች መምህራንን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆችን፣ ወደ ጎን በመተው በ1986 ዓ.ም (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ) በዓለም ባንክና በዓለም የገንዘብ አባዳሪዎች ድርጅቶች እገዛ የይድረስ ይድረስ የትምህርት ፖሊሲ ቀርጾ በተግባር አውሏል። ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ በወቅቱ በኢመማ ከፍተኛ ተቃውሞ ደርሶበት ተግባራዊ ሳይሆን የቀረው ሴክተር ሪቪው በመባል ይታወቅ የነበረው የትምህርት ክላሳ ፕሮግራም በ1963-64 ዓም( እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ) ተዘጋጅቶ የነበረው ትምህርትን በፍላጎቷ ስር ለማድረግ ከፍተኛ ጫና ታደርግ በነበረችሁ በአሜሪካ የሚመራው የዓለም ባንክ አማካኝነት ነበር። ይህ በ82 "ኤክስፓርቶች" ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ አቅድ ወጥቶለት የነበረው የትምህርት ክላሳ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያላስገባ ፣ መምህራን፣ ወላጆችና ተማሪዎች ያልተሳተፉበት ነበር።

በዚህ ወያኔ ቀርጽኩት በሚለው የትምህርት ፖሊሲ የተነሳ የትምህርቱ ጥራት ከመሻሻል ይልቅ ቀድሞ ከነበረበት በባሰ ሁኔታ እንዲዘቅጥ እድገቱንም ቁልቁል እንደካሮት እንዲሆን አድርጓል። ስለሆነም የወያኔ የትምህርት ፖሊሲ ትውልድ ገዳይ መሆኑ ከተነገረ ዓመታት ተቆጥረዋል። የወያኔ መንግስት በዘረጋው የት/ፖሊሲ በመግፋት ውድቀቱን በተለያዩ ምክኒያቶች በመሸፋፈን ለውድቀቱም ተጠያቂ መምህራን እንደሆኑ በተለያዩ ጊዜያት በየዓመቱ ከመምህራን ጋር በሚያደርገው አሰልቺ ውይይት አስተጋብቷል። አንድ ጊዜ " የትምህርት ንቅናቄ" ሌላ ጊዜ ደግሞ " ጥልቅ ተሐድሶ" ወ.ዘ.ተ በማለት መምህራንን፣ ወላጆችን፣ ተማሪዎችንና በእጠቃላይ ሕብረተሰቡን ሲያደናቁር ከርሟል። መምህራን ለወያኔ የውሸት ክስ ቦታ አልሰጡም።

የችግሩ መንስሔ ከመነሻው ከስሩ የትምህርት ፖሊሲው መሆኑ እየታወቀ የመርሀ ትምህርት (Syllabus) ለውጥ በማድረግ ሥርዓተ ትምህርቱ እንደ ተለወጠ አድርጎ ማቅረቡም ይታወሳል። የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ሣይደረግ የመረጃ መጻሕፍት ለውጥ በተደጋጋሚ ማድረግ እንደ መፍትሔ ተደርጎም ተወስዷል። በአንድ የትምህርት ዘመን ለአንድ ዓመት እንኳን ሳያገለግሉ በሌላ መፃህፍት መተካት ፣ የተዘጋጁትም ቢሆኑ በመምህራን አስተያየት ያልዳበሩ በመሆናቸው ከመሻሻል ይልቅ ውድቀቱ ሊፋጠን በቅቷል። በወያኔ የምህርት ሚኒስቴር ዘገባ መሰረት በአንድ ወቅት ለህትመት ብቻ 150 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር እንደወጣ ተገልጿል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀረጥ መልክ ለትምህርት የከፈለውን አንጡራ ሀብት እንዲባክን አድርጓል።

በመማር ማስተማር ስራ መምህራን አድማጭ እንጂ ተሣታፊ ባልሆኑበት ፣ መምህራን ሳይፈሩ ፣ ሳይሸማቀቁ ፣ ሀሳባቸውን የመግለጽ መብታቸው በተገፈፈበት፣ መብታቸውን ለማስከበርና ትምህርት በጥራት ለህዝብ ልጆች በዕኩልነት እንዲሰጥ በሚጠይቁ መምህራን ላይ ግድያ፣ እስራት፣ ሰውሮ ደብዛ ማጥፋት፣ ከስራ ማሰውገድ ባልቆመበት፣ ለመምህራን ምቹ የማስተማሪያ ሁኔታ ባልተፈጠረበት፣ የመምህራን የደመወዝና የሌሎች የመብት ጥያቄዎች ምላሽ ባጡበት፣ ባንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች ከአስረኛ ክፍል ወደ ሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ማላፍ ያልቻሉ ተማሪዎች ያለምንም ስልጣና እንዲሁም ከመምህራን ተቋም ስልጣናቸውን ያልጨረሱ ተማሪዎች መምህራን በሆኑበት፣ የትምህርት አስተዳደሩ ልምድ በሌላቸው ካድሬዎች በተያዙበት ፣ የመምህራን ምልመላና ስልጣና በችሎታ ሳይሆን በፖለቲካ ታማኝነት በሆነበት፣ መምህራን ባልተሳተፉበት ፣ ባለመኑበት፣ ባልተቀበሉት የትምህርት የት/ፖሊሲ በግዳጅ እንዲያስተምሩ በሆነበት፣ ሙያ ማህበራቸው በተላጣፊ ተነጥቆ የመምህራን ገንዘብና ንብረት በሚዘረፍበት ሁኔታ፣ የትምህርት ምዛናና

ግምገማ ዘርፉ በባለሙያዎች ሳይሆን ለዚህ ዘርፍ እውቀት በሌላቸው ካድሬዎች እጅ ገብቶ ባላበት ሁኔታ( የአገር አቀፍ ፈተናዎች ስርቆትን ይመለከታል) እና ለአገር እድገትና ለትምህርት ጥራት ፋይዳ በሌላቸው፣ የትምህርት ስብሰባዎችና ኮንፍረንሶች ስም ወያኔን ስልጣን ላይ ለማቆየት በካድሬዎች በሚዘጋጁ የፖለቲካ ስብሰባዎች የትምህርት ክፍለ ጊዜ በሚባክንበት በአጠቃላይ የትምህርት ፖሊሲው ሆን ተብሎ አገርንና ህዝብን ለመጉዳት ተግባራዊ ሆኖ ባላበት ሁኔታና የመምህራን የአካዳሚክ ነፃነት በጠፋበት የትምህርት ጥራት ከቶዉኑ ሊታሰብ አይችልም። ለትምህርት ኢንዱስትሪ ኪሳራ ተጠያቂው የወያኔ አገዛዝና የቀረጸው ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊሲው ነው።
ለአብነት ያህል፡ የብሔራዊ ባንክ አማካሪ የሆኑት አቶ ኢያናቸው አሰፋ በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በተመለከተ ባደረጉት ጥናት መሰረት በ2014ና በ2015 ዓ.ም ( እንደ አውሮፓ አቆጣጠር) በአገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች በረዳት መምህርነት ለማገልገል በውድድር ይሁን ተብሎ 10ሺ ተመዘገቡ። ( ቀደም ሲል ከ1997ዓ.ም ምርጫ በኋላ የመጀመሪያ ዲግሪ ያገኙና የተመረቁ ለሁለተኛ ዲግሪ ለመማር የወያኔ ደጋፊ ድርጅቶች አባል መሆን ግዴታ ነበር)
ከተመዘገቡት ውስጥ 716 ተመረጡ ። በጥናቱ መሰረት ከተመረጡት ከ716 ውስጥ በሠለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ ዓይነት ከ80% በላይ ያገኙት 1 ፐርሰንት ብቻ ሲሆኑ ከነዚሁ ከ716 ውስጥ 28 ፐርሰንት የሚሆኑት ደግሞ ያገኙት ውጤት ከ70-79 ነው። ከተወዳዳሩት ውስጥ አማካይ ውጤታቸው 57.8 ሲሆን ይህ ደግሞ በእጅጉ አነስተኛ ነው። ከተወዳዳሩት መካከል 127 ወይም 1/5 ኛ የሚሆኑት ደግሞ በሰለጠኑት ትምህርት ( Major subjects ) ያገኙት ውጤት ከ50 ፐርሰንት በታች ነው።
እንዲሁም በ2015 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ100 አፍሪቃ አገሮች ውስጥ በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በተደረገው ሌላ ጥናት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብቻ 50ኛ ደረጃ ላይ ሲገኝ ሌሎች በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ዩኒቨርስቲዎች ከነአካቴው ስማቸው አልተጠቀሰም። እንዲሁም በ2016ም ሌላ አንድ ጥናት በዓለም ውስጥ ያሉት ዩኒቨርስቲዎች የዩኒቨርሲቲ ደረጃ የጠበቁ መሆናቸውን ለማወቅ ባደረገው ጥናት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ዩኒቨርስቲዎች በሙሉ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ጨምሮ የዩኒቨርስቲ ደረጃን ያልጠበቁ መሆናቸውን አረጋግጧል።
ታዲያ ችግር ፈቺ የሰለጠነ የሰው ኃይል ተመረተ? እነኝህ ናቸው ችግር ፈቺ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማምራት የተዘጋጁት? ከመነሻው ከአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ባሉት የትምህርት አሰጣጥ ፈተና ሳይፈተኑ ከአንዱ የክፍል ደረጃ ወደ ሌላኛው የክፍል ደረጃ በጅምላ እንዲያልፉ እየተደረገ ) ሆሄያት ሳይለዩ ወደ ሚቀጥሉት ክፍሎች እንዲዛወሩ ተደርጎ በመለስተኛና በሁለተኛ ደረጃዎች ደግሞ ለክፍል ደረጃዎቹ የሚመጥን እውቀት ሳይገበዩ እየተገፉ ሄደው የዩኒቨርስቲ ተመራቂ ሆኑ የምርቱ መጨረሻ ይሄ ነው። ወያኔ ኢትዮጵያን በትምህርቱ ዘርፍ ለማጥቃት የፈጸመው ትልቅ አገራዊ ወንጀል ውጤት ይህ ነው።
የትምህርት ኢንዱስትሪ ኪሣራ ውስጥ እንደተዘፈቀ ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች በግልፅ ያሳያሉ። ለትምህርቱ ውድቀት ተጠያቂ ወያኔና የወያኔ የት/ፖሊሲ ነው። የወያኔ አገዛዝ ግን በየጊዜው በሚያደርገው ስብሰባ የትምህርቱ ጥራት እንደወደቀ ተቀብሎ ለውድቀቱ ግን ተጠያቂው መምህራንና ተስፋ የቆረጠው ትውልድ ነው በማለት ያላዝናል።የአብዬን ወደ እምዬ ልክክ ይሏል ይህ ነው።

የትምህርት ውድቀት የአገርና የሕዝብ ውድቀት ነው። ስለዚህ አገራችንን ከወድቀት ሕዝባችንን ወያኔ አደንቁሮ ለመግዛት ካላው እርኩስ ፍላጎት ማዳን የሚቻለው ምልዓተ ሕዝቡ ተደራጅቶ የተጀመረውን ሕዝባዊ አመፅ በማስፋፋት የወያኔን ዘረኛ ሥርዓት አስወግዶ በምትኩ ፍትሕ ርትዕ የሰፈነበት በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲገነባ ነው።
መምህራን መብቶቻቸውን ለማስከበር የትምህርቱንም ጥራት ለማስጠበቅና አገራችንን ከውድቀት ለመታደግ ትግላቸውን ከተማሪው፣ ከሠራተኛው ከአርሶአደሩ በአጠቃላይ መብታቸውን ለማስከበር ከሚተጋሉ ወገኖች ጋር እንዲያቀናጅ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ በድጋሚ ጥሪ ያቀርባል።

ትግሉን ከግቡ ለማድረስ ፣ መደራጀት መደራጀት አሁንም መድራጀት!!!
ለትምህርት ውድቀት ተጠያቂው ወያኔና ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊሲው ነው!!!
መምህራን መብታቸውን በትግላቸው ያስከብራሉ!!!